# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 31 ቁ.1 ነሐሴ 1998


## የት ደርሰናል- ወቅቱስ ምን ይጠይቀናል?

ዛሬ በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ "አቤቱ አምላኬ፥ የአበሳችን የማለቂያ ጊዜው መች ይሆን? ከዚህስ የባሰ ምን ይመጣብን ይሆን" በማለት የሚገረሙና የሚጠይቁ ብዙ ዜጎች እንዳሉ የሚታወቅ ነው፡፡ ጥያቄዎቹን ለያይቶና ከፋፍሎ መመለስ ወይም ማብራራት ባይሞከርም፥ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና ተራማጅ ኃይሎች፥ በተለይም ኢሕአፓ፥ በረጅም የትግል ዕድሜው ውስጥ ከታገለላቸው መሠረታዊ የኤኮኖሚ፥ የፖለቲካ፥ የማኅበራዊና ሌሎችም ጥያቄዎች ጋር እያገናዘቡ መመልከት ሊረዳ ይችላል፡፡ በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ፥ ከሕዝባችን ዘጠና ከመቶ በላይ የሚሆነው ሲራብ ጠግቦ በልቶ ያደረበትን፥ ሲጠማ ጠጥቶ የረካበትን፥ ሲታመም ታክሞ የዳነበትን፥ ሲታረዝ አሚልቶ የለበሰበትን ወቅት ለማስታወስ እንቸገራለን፡፡ በአንጻሩ፥ ችግር ችግርን እየወለደ፥ አንዱ በሽታ ለሌላው በሽታ እያስረከበ፥ የአምናውና የሃቻምናው ረኀብ ያደቀቀው አካል ሳያገግም የዘ ድሮው ረኀብ እየተተካና የተረፈውን መንጠራወዣ ኃይሉን እያጠነፈፈበት፥ በሽብር የታጀበው ጭቆናና መረን የለቀቀው ምዝበራም ምሬትንና ጥላቻን እየቀፈቀፉ መሄዳቸውን ግን በየእለቱ እንታዘባለን፡፡

ምነው፥ ሕዝባችን ከዚህ የችግር አዙሪት መውጣት አቃተው? ብዙው ኢትዮጵያዊ ከልቡ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው፡፡ ታዲያ ማንኛውም ሕዝብ ሁኔታዎች እስከተመቻቹለት ድረስ ቀይደው ከያዙት የእድገት መሰናክሎች እራሱን ለማላቀቅ አይችልም የሚል እምነት የለንም፡፡ ሕዝባችን ደግሞ፥ መከራን የሚችልና የኑሮንም ውጣውረድና እንግልት በታታሪነቱ አቸንፎ የሚያድር ለመሆኑ ምስክር አያሻውም፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የግብረ-ሠናይ ተቋማትን ማንቀሳቀስ የኑሮ መተዳደሪያቸው ያደረጉት የውጭ አገር ሰዎች እንኳን ይህን ሐቅ ለመደበቅ አልፈለጉም፡፡

ኢሕአፓ ይህንን የህዝባችንን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ተብትበው የያዙትን ሰው ሰራሽ የችግር መንስኤዎችን ለማስወገድ ይቻላል ብሎ በማመን የዛሬ ሠላሳ አራት ዓመት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገባውን የትግልና የመስዋዕትነት ቃል ኪዳን በቅርቡ ሚያዚያ 1998 ዓም ባካሄደው አራተኛ ጉባዔው ወቅትም አድሶታል፡፡ ይህ ጉባዔ፥ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ነባራዊና አዲስ በመፈጠር ላይ ያሉትን ልዩ ልዩ የኤኮኖሚ፥ የፖለቲካና የማሕበራዊ እውነታዎችንና ክስተቶችን በጥሞና በመርመር፥ በሶሻል ዴሞክራሲ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ፕሮግራሙ ክልል ውስጥ ሊደረጉ የሚገባቸውን መስተካከሎች አድርጓል፥ አቋሞች ወስዷል፥ ለተለያዩ በተግባር ለሚሰማሩ ክፍሎችም መመሪያ ሰጥቷል፡፡ ቀደም ብለው የነበሩት ሁሉን አቀፍ ችግሮችና ካለፉት አምስት አመታት ወዲህ፥ ዘመነ ሽብር እንበለውና፥ የተከሰቱትን አለም አቀፋዊና አካባቢያዊ ችግሮች በጋራ ለመቋቋምና ለመታገል፥ ብሎም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሠላም አግኝቶ የኑሮ ውጥረቶቹን በተረጋጋ ሁኔታ ሊቋቋማቸው እንዲችል፥ ካሁን ቀደም ሲከተለውና ሲሠራበት የቆየውን የኅብረት የፖለቲካ

መስመር በማጠንከር፥ የመዋቅር መስተካክል አድርጓል፥ የተሻሻለ የሥራ መመሪያ አውጥቷል። በዚህም መሠረት፥ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና በሕዝቧ አንድነት ላይ የተመሰረተ የኢትዮቶጵያ የተቃዋሚ ኃይሎች (በሙያና በተለያዩ ሲቪክ ማኅበሮች የተደራጁና ገና ያልተደራጁትንም ኢትዮጵያውያንን ትርጉም ባለው መንገድ የሚያካትት) ትብብር እንዲመሠረትና እንዲጸብር፥ ለዚህም መሳካት፥ የበኩሉን ጥረት እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል።

ለኅብረት የፖለቲካ መስመርና ትግል ያለውን ታማኝነትና ለከፈለው መስዋዕት ድርጅታችን መረጃ ለማቅረብ ሊገደድ አይገባም። ለመጀምሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ ለታየው የኅብረት ፖለቲካ ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) ፥ ተከትለው ለነበሩት ልዩ ልዩ ሙከራዎችና በመጨረሻም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) መመስረት ለተጠናቀቀት የኅብረት እርምጃዎች የኢሕአፓ ብርቱ ጥረቶችና አስተዋጽዖዎች የሚዘነጉ አይሆኑም። ኢሕአፓ ለምን በህብረት ግንባር ምሥረታና በኅብረት ትግል ላይ እንዲህ አተኮረ ቢባል ባጭሩ፥ ከላይ እንደተጠቀሰው፥ አሁን በአገሪቱ ውስጥ ያሉትና በአዲስ እየተከሰቱ የሚገኙት የኤኮኖሚ፥ የፖለቲካና የማህበራዊ ችግሮችን ለማስወገድ መካሄድ የሚገባቸው የትግል ዓይነቶች ዘርፈ-ብዙ፥ መጠነ-ሰፊና ውስብስብ በመሆናቸው ነው።

ይህም ማለት፥ ዛሬ የሚደረገው ትግል አገርን የማዳን ትግል ነው ማለት ነው። አገርን የማዳን ትግል ደግሞ የሚገለጠው፤ (1) አገሪቱ የገባችበትን የኤኮኖሚ አዘቅት በውል ተገንዝቦ እንዴት ሁኔታውን ለመቀልበስ እንደሚቻል ከወዲሁ በመረዳት፥ (2) በሕዝቡ ላይ የተጫኑትን ኋላ ቀርና ምስቅልቅል የዘር የፖለቲካ ችግሮችን ተረድቶ መፍትኄዎቹን በመሻት፥ (3) ሕዝባችንን እየፈጁ ያሉትን ቀሳፊ በሽታዎች ለመግታት ዘዴዎችን በመትለም፥ (4) የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለፈቃዱና ያለፍላጎቱ በማይመለከተውና በማይጠቅመው የጦርነት እልቂት ውስጥ ተጠልፎ ሊገባ መሆኑን በመረዳትና በመከላከል፥ (5) እነኝህን ብሔራዊ አደጋዎች በሙሉ እንደ አንድ ሕዝብና እንደ አንድ ኃይል ለመወጣትና የኢትዮጵያን ብሔራዊ ክብር መልሶ ለማረጋገጥ የኅብረት ትግል አማራጭ የሌለው መሆኑን በማመን ነው።

በአንድ ኅብረተሰብ የእድገት መለኪያዎች፥ ለምሳሌ በሕዝቡ አማካይ ዓመታዊ ገቢ፥ በትምህርት፥ በጤና፥ በህይወት እርዝማኔ ሲመዘን፥ ኢትዮጵያ፥ የዛሬ አርባ ዓመት ከነበረችበት ደረጃ በታች እንደምትገኝ የተባበሩት መንግሥታት ልዩ ልዩ ተቋሞች ሳይቀሩ ይገልጻሉ። ከአርባ ዓመት በፊት እንደ ሕዝቡ አማካይ ዓመታዊ ገቢ ሲጠቀስ የነበረው $110 (ኢ.ዶ.) 990 ብር ዛሬ ወደ $90 (ኢ.ዶ.) 810 ብር አሽቆልቁሏል፥ እንዲያውም አንዳንዶቹ ወደ $86 (ኢ.ዶ.) 774 ብር አውርደውታል። ኢትዮጵያ በኤኮኖሚ እድገት ከዓለም አገሮች የመጨረሻዋ ናት የሚባለው ነገር ሊደንቀን የማይገባው፥ ባለፉት አሥራ አምስት ዓመታት ውስጥ አገሪቱ ያስመዘገበችው አማካይ የኤኮኖሚ ዕድገት 1.9% ሲሆን፥ እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር፥ ከ1983 እስከ 1996 ድረስ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ደግሞ በአማካይ በየዓመቱ 2.8% ስለሆነ ነው። ይህ የሚያመለክተው አንድ ቀላል፥ ነገር ግን ጠቃሚ የሆነ፥ ቁምነገር ቢኖር፥ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከኤኮኖሚ ዕድገት ከበለጠ የሕዝቡ ኑሮ ደረጃ፥ በሁሉም መልኩ፥ ሁልጊዜ ወደታች እያሽቆለቆለ እንደሚሄድ ነዉ።

ይሄ የሕዝባችን የኑሮ ደረጃ ማሽቆልቆል እንዲሁ በአጋጣሚ የመጣ ዕጣ ፈንታችን ወይም ተፈጥሮ ባስከተለው ጉዳት የደረሰብን ብሔራዊ አደጋ አይደለም። አገራችን ኢትዮጵያ፥ የተፈጥሮ ሀብቶች ባለጸጋና ለኤኮኖሚ ዕድገቷ በሚያመች ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ የታደለች አገር ነች። ነገር ግን የተፈራረቁባት ገዥዎቿ፥ በተለይም የመለስ አምባገነናዊውና አሸባሪው አገዛዝ ቡድን መሪዎች በግልና በቡድን ጥቅሞቻቸው የታወሩና ለመላው ሕዝቧ ዘላቂ፥ ሰላማዊና ሁለንተናዊ ዕድገትና የተደላደለ ኑሮ የማያስቡ በመሆናቸው ነው። ስለዚህ

ሕዝባችን ዛሬ በማያቋርጥ ድኽነት፥ በማያባራ የረኀብ ቸነፈር፥ በማይቆም ቀሳፊ በሽታና በሚያሽማቅቅ ብሔራዊ ሀፍረት ውስጥ ይገኛል።

ይህንኑ የአገሪቱን የኤኮኖሚ ችግር በሌላ መልክ ብናስቀምጠው አስደንጋጭ ሥዕል እናያለን። የከተማ ነዋሪ ከሆነው ሕዝባችን ውስጥ በመንግሥትና በግል የኤኮኖሚ ተቋማት ውስጥ ተቀጥረው በደሞዝ የሚተዳደሩት ከጠቅላላው ሕዝባችን ውስጥ 6% ብቻ ናቸው። ወደ 80 ከመቶ የሚጠጋውንና በገጠር በእርሻ ተዳዳሪነት የሚኖረውን ሕዝባችን ሁኔታ ስንመለከት የአገሪቱ የእርሻ ዕድገትና የገበሬው የኑሮ ደረጃ ለመሻሻል ምንም ዕድል የላቸውም። የመለሰ አገዛዝ ለፖለቲካ አላማው እንዲያመቸው ማለትም ገበሬውን መሉ ለሙሉ ለመቆጣጠር እንዲያስችለው (ገበሬው) ሊያርሰው የሚችለውን መሬት በመንግሥት ባለቤትነት ይዞታል። ይህ ዓይነቱ የመሬት ስሪት የተረጋገጠ የርስት ባለቤትነት ስለማይሰጥ ለእርሻ ዕድገት እንደማይረዳና የሀገሪቱን የተፈጥሮ አካባቢን እንዲሸቀለቆል እንደሚያደርግ በአገራችንና በሌሎች አገሮችም ተመልክተናል፥ ብዙ ምሁራንና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት ጥናታዊ መረጃዎችን አቅርበዋል።

እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለበት ዘረኛና አድሎአዊ የሆነው የመለስ ቡድን የኤኮኖሚ ፖሊሲ በአጠቃላይ በሀገር ደረጃ ለኢትዮጵያ ዕድገትና ልማት ብሎ የታቀደ አይደለም። ምናልባትም ለማስመሰል ይሞክር ይሆናል እንጂ ኢትዮጵያ እንደሀገር ውድም ብትል ደንታ እንደሌለው ኤኮኖሚው የፖለቲካው ነጸብራቅ በመሆኑ ብዙ ምርምር አያሻውም። ጥበቱንም ሲያንጸባርቅ ለትግራይ ክልል የሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች፥ የዕድገት ፕሮግራሞችና የእርዳታ አደላደሎች ለሌሎች ክልሎች ከሚጠቀምባቸው ይለያሉ። ያም ሆኖ በትግራይ የሚኖረው ሕዝባችንን የኑሮ ደረጃ በመሠረቱ አልቀየረውም። ባጠቃላይ እነዚህ ጎጂ የሆኑት የኤኮኖሚ ፖሊሲዎቹ፥ በተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም የ1997 ዓ.ም ሪፖርትና አሃዝ መሠረት፥ ላለፉት አሥራ ሦስት ዓመታት በአማካይ 9.6 በመቶ ዓመታዊ የዋጋ ግሽበት እየታገዙ አጠቃላይ ድኽነትንና ረኀብን በአገሪቱ ለማስፋት ችለዋል። እንዲሁም በአገራችን የኑሮ ደረጃ መለኪያዎች መሠረት በፍጹም ድኽነትና በከረረ ረሀብተኝነት ውስጥ የሚገኘው የሕዝብ መጠን 57 በመቶ ነው። ከአሥራ አምስት ዓመት ዕድሜ በላይ ከሆኑ ኢትዮጵያዊያን ውስጥ 42 በመቶው መጻፍና ማንበብ አይችሉም፥ 76 በመቶ ኢትዮጵያዊያን አስተማማኝ የውሃ አቅርቦት የላቸውም። 88 በመቶ ኢትዮጵያዊያን ለጤናቸው አስፈላጊ የሆኑ ዕጻታቸውን ለመጠበቅ የሚገለገሉባቸው ነገሮችን ለማሟላት አቅሙ የላቸውም። ከአጠቃላዩ የመንግሥት በጀት ለሕዝቡ የጤና ግልጋሎት የሚመድበው 6 በመቶ ሲሆን ለትምህርት ደግሞ ከ16 በመቶ በታች ነው።

እነኝህ ሁሉ ማኅበራዊ ግልጋሎቶች በመንግሥት ዓመታዊ ባጀትና ፕላን ውስጥ ቅድሚያ በማግኘት የሕዝቡ አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል ያልተደረገበት ምክንያት እንዲያው እንደ ዕድል የሆነ ወይም የአገሪቱ የሃብት ምንጭ በቂ ስላልሆኑ አይደለም። ከላይ በአሀዝ የቀረቡት ማኅበራዊ ግልጋሎቶች በሙሉ ደግሞ ለአንድ ኅብረተ-ሰብ ለጤናማና የተደላለደለ ኑሮው በጣም አስፈላጊ ናቸው። ይህ ዘረኛና ጎጂ የኤኮኖሚና ማኅበራዊ ፖሊሲ የሚያስከትላቸው ችግሮች ሊገቱ የሚችሉት በተደራጀና በተባበረ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ብቻ ነው። የኢትዮጵያዊያ ሕዝብ ትግል ደግሞ በአጠቃላይ ሲታይ አገርንና ህዝብን የማዳን ትግል ነው። ስለዚህ፥ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች የኅብረት ትግል ይህንን አገርንና ሕዝብን የማዳን ትግል የሚያግዝ፥ የሚመራ መሆን ይኖርበታል። ይህ ለነገ የማይተላለፍ ወቅታዊና አንገብጋቢ የአገር ጉዳይ ነው።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አሸባሪውና ጠባቡ የመለስ ቡድን የፈጠራቸው አዳዲስ የኤኮኖሚና ማኅበራዊ ችግሮቻችን ከሞላ ጎደል ይህ ቡድን በሕዝባችን ላይ የጫነው ሕዝብን ከፋፋይ ፖለቲካ ውጤትና ነጸብራቅ ናቸው። እስከዛሬ ድረስ ይህ ጠባብ አምባገነን ቡድን ብሔረሰቦችን በመከፋፈል ላይ የተመሠረተ ፖለቲካው ያደረሳቸው ሁለንተናዊ ችግሮችና ለወደፊቱም በሕዝቦች መሀል ጥሎአቸው የሚያልፋቸው ጠንቆች በሰፊው ተጽፎባቸዋል፥

ሰፊ ትንተናና ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ ሆኖም፥ ተደጋግሞ መታወስና መነገር ያለበት ቁልፍ ነገር፥ ወያኔ እንደ ዓላማውና የፖለቲካ ግቡ የያዘው፥ የኢትዮጵያዊነት ስሜትንና አስተሳሰብን ማፍረስና ማጥፋት መሆኑ ነው፡፡ ካሁን ቀደም በተደረጉት የዴሞክራሲ፥ የፍትኅና የእኩልነት ትግሎች ውስጥ የነበረው ዋናው ትኩረት በወቅቱ ሰፍነው የነበሩትን የመደብ፥ የጎሳ፥ የሃይማኖትና የጾታ ጭቆናዎችን አስወግዶ በምትካቸው በእኩልነት፥ በመከባበርና በመፈቃቀድ ላይ የተገነባች ኢትዮጵያን መመሥረት ስለነበረ፥ ከጠባብ ብሔረተኞች በኩል በኢትዮጵያ ላይ ያንዣብብ ለነበረው አደጋ ብዙ ትኩረት ተፎካካሪ ከነበሩት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች አልተሰጠም፡፡ ዛሬም ቢሆን፥ ሰፋና ላቅ ባለው ብሔራዊ የፖለቲካ፥ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ አጀንዳዎች ላይ ተደራጁ የምንላቸው ኅብረ-ብሔር የአንድነት ኃይሎች ይህንን አደጋ በውል ተረድተውት በጋራ ለመመከት ሁሉም ተነስተዋል ለማለት አያስደፍርም፡፡

እራሱን ህወሓት ብሎ የሚጠራው ጠባቡ የነመለስ ቡድን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ክብርና ሉዓላዊነት አስከብሬ የዜጎችዋን ደህንነትና ዕድገት ለማራመድ የተነሳሁና የመጣሁ ኢትዮጵያዊ ኃይል ነኝ (ተሳስቶ እንኳን) ያለበት አንድም ጊዜ የለም፡፡ አሁንም፥ እስከዛሬ ድረስ፥ ስሙ እንደሚያመለክተው፥ በያዘው መልክ ኢትዮጵያን ለመቆጣጠርና ለመቦጥቦጥ ካልቻለ፥ ትግራይን ነፃ ለማውጣት የተሰለፍኩ "ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ" ነኝ ነው የሚለው፡፡ ኢትዮጵያን ተቆጣጥሮ ለመቆየት የሚጠቀምበት ዋና መሳሪያው ደግሞ፥ ኢትዮጵያውያንን በብሔረሰብ በጎጥና በሃይማኖትም በመከፋፈል በጋራ ለጋራ ጥቅማቸው እንዳይነሱበት ማድረግ ነው፡፡ ይህ እስካሁን ድረስ ግልጽ ካልሆነ፥ በተለጣፊነት ያደራጃቸውንና የኮለኮላቸውን ቁጥር ስፍር የሌላቸውን የብሔረሰብና የጎጥ (ተለጣፊ) ድርጅቶችን መመልከቱ ብቻ ይበቃል፡፡ በዚያ ላይ ያፈራረሳቸውን ለኅብረተሰቡ ጠቃሚና ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተቋሞችንና መዋቅሮችን መቁጠሩ ሌላው ይህንኑ ገላጭ ነው፡፡

አሸባሪው የነመለስ ድርጅት ከአቅሙ በላይ እስካልሆነበት ድረስ ምንም ነገር ለአጋጣሚ የማይተው መሰሪ ድርጅት ነውናም ይህ ከፋፋይነቱ ኢትዮጵያን በጫማው ስር አፍኖ ለማቆየት የማያስችለው ከሆነ ደግሞ ለአፈና ስትራቴጂው የሚጠቀምባቸውን የወታደራዊና የደህንነት (የሴኪዩሪቲ) መዋቅሮቹን ድምጹን አጥፍቶ ሲያደራጅ እንደነበረ የግንቦቱ 1997 ዓ.ም. ምርጫ አሳይቶናል፡፡ ህዝቡ ድምጼ ይከበር ብሎ በሰላም አቤቱታውን ባሰማበት የምርጫው ማግስት፥ በአዲስ አባባና በሌሎች ከተሞች ውስጥ፥ የፋሺስት ጽልመት በኢትዮጵያ ላይ የጣለውንና ለግድያ ብቻ ሲሰለጥን የቆየውን "አግዐዚ" የተባለውን ጨፍጫፊ የጸጥታ ኃይል ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ይህ በብዙ ሰላማዊና ራሳቸውን ተከላክለው ማዳን በማይችሉ ኢትዮጵያውያን ደም የተነከረ የግድያ ኃይል የተመለመለው ከሞላ ጎደል ከተወሰነ ክፍል ብቻ መሆኑ ከግምት ውስጥ መግባት ቢኖርበትም፥ ወያኔ ለምን ይህን እንዳደረገ መመርመርና መጠራጠር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ከትግራይ ውጭ በሌሎች ከተሞችና የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚኖሩትን የትግራይ ተወላጆችን ጨምሮ፥ በጎሳ፥ በሃይማኖት፥ በጾታ፥ በዕድሜ ሳይለያይ በአንድ ድምፅ ወያኔን ከጎሳና ከዘር ፖለቲካው ጋር ወግድ ያለበት የግንቦቱ ምርጫ ብዙ አስተምሮናል፡፡ በትግራይ ክልል የሚኖረውም ህዝባችን የነመለስ አሸባሪ ቡድን ጥብቅ አፈና ሰለባ በመሆኑ እንጂ እንዳለ ወያኔን አፍቅሮ መረጠው ማለት አይደለም፡፡ ይህ በኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ልዩ ሥፍራና ምዕራፍ የሚይዘው የግንቦት 7 1997 ምርጫ ግልጽ ያደረጋቸው በርካታ መሠረታዊ ቁም ነገሮች አሉ፡፡ አንደኛ፥ እስካሁን ድረስ ይጠራጠሩ ለነበሩ ሰዎች፥ ቡድኖችና ድርጅቶች የነመለስ ጠባብና አምባገነኑ ቡድን በምንም መልኩ ይሁን በምንም፥ በሰላማዊ የፖለቲካና የመንግስት ልውውጥ አለማመኑን፤ ሁለተኛ፥ የኢትዮጵያ ህዝብ ሰብአዊ መብቶች መረገጥ ይሁን የህዝቡ መጨፍጨፍ፥ መታሰር፥ መሳደድ፥ መሰቃየት ለውጭ አገር መንግስታት መዘዙ የእነሱን ጥቅም እስካላሰጋ ድረስ ደንታ እንደማይሰጣቸው፤ ሦስተኛ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የሚቆሙት ኢትዮጵያውያን ራሳቸው ብቻ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህ በአጭር ሲጠቃለል፥ የትግሉ ሜዳ

ኢትዮጵያ፥ የትግሉ የቆሳቁስና የፖለቲካ ድጋፍ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን፥ የትግሉ የሰው ኃይል ኢትዮጵያዊያን ማለት ብቻ ነው:: ለዚህ ነው እንግዲህ ለኢትዮጵያ አንድነት የሚቆሙት ተቃዋሚ ኃይሎች የኅብረት ትግል ለነገ የማይተላለፍ አንዱ ዓቢይ አገራዊ ጉዳይ ነው የምንለው::

በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በነመለስ አምባገነን ቡድን የተቃጡት አደጋዎች ከላይ በተዘረዘሩት ውስጣዊ በደሎችና ጭቆናዎች ብቻ አልተወሰኑም:: ኢትዮጵያ በዚህ ጠባብ ቡድንና በውጭ አጋሮቹ ተጠልፋ ሊከስም በማይችል በአካባቢያዊና ሃይማኖታዊ የጦርነት ረመጥ ውስጥ እንድትጋይ እየተደገሰላት ነው:: ኢትዮጵያ፥ እስከዛሬ ድረስ ከወሰንዋ አልፋ ሌሎች አገሮችን፥ የጎረቤት ይሁን የሩቅ፥ በመውጋት የምትታወቅ አገር አይደለችም፥ የወጋችበት ጊዜም በታሪኳ ውስጥ የለም:: ድንበሯ ተደፍሮ በሌሎች አገሮች ስትወረር እንኳን ወራሪውን ኃይል ከማባረርና ዳር ድንበሯን ከማስከበር ሌላ የተቸነፈውን ወራሪ ጦር ተከታትላ ወሰን ጥሳ ያቸነፈችውን ሀገር የወረረችበት ወቅት የለም:: ኢትዮጵያ በአካባቢዋ ካሉት አገሮች ጋር መልካም ጉርብትና ከመሻት በስተቀር ጠብ ጭራ አምባጓሮ የቀሰቀሰችበት ወይም ጦርነት የፈጠረችበት ጊዜ አልነበረም:: አንዳንድ የጎረቤት አገሮች፥ በተለይ ሱዳንና ሱማሌ፥ የኢትዮጵያን ሰላም የሚበጠብጡ ተግባራት ሲፈጽሙ ወይም ውስጣዊ ችግሮችንና ጦርነቶችን ሲቀሰቅሱና ሲረዱ እንኳን፥ ኢትዮጵያ ድንበር አልፋ አጸፋዊ እርምጃዎችን ወስዳ አታውቅም::

ዛሬ ግን፥ ይህ የኢትዮጵያ የመልካም ጉርብትና ፖሊሲ በአምባገነኑ የነመለስ መንግሥት ተቀይሮ፥ በወያኔ የሚታዘዘው ጦር እስከ መሀል ሶማሊያ ዘልቆ ገብቷል:: በርግጥ፥ በሶማሊያ ውስጥ በጦር ኃይል እየተጠቀመ በአክራሪ የእስልምና ሃይማኖት የፖለቲካ መመሪያነት ላይ የተመሠረተ መንግስት ልንወድና ልንደግፍ ከቶውንም አይቻልም፥ አይታሰብም:: በተጨማሪም፥ ይህ መንግሥት ለመመሥረት በመውተርተር ላይ ያለ የአክራሪ እንቅሥቃሴ ቡድን የግዛት ይገባኛልን ጥያቄ በኢትጵያ ላይ ማንሳቱን ባለማወላወል አጥብቀን እናወግዛለን፥ አምርረንም እንቃወማለን:: በአንጻሩ ግን፥ በሶማሊያ ውስጥ የሚመጣውን መንግሥት፥ ሃይማኖታዊ ይሁን ከማንኛውም ዕምነት ነጻ የሆነ ፥ የመቀበልና የመደገፍ ወይም የመቃወምና የማስወገድ መብትና ምርጫ የሶማሊያ ሕዝብ ብቻ ነው ብለን እናምናለን:: ማንኛውም የውጭ መንግስት፥ በኢትዮጵያ ውስጥ በሕገ-ወጥነት እንደ መንግሥት የተቀመጠውን አሸባሪውን የነመለስ ቡድን ጨምሮ፥ በሶማሊያ የውስጥ ጉዳይ በምንም መልኩ ጣልቃ ለመግባት መብት የለውም፥ የዓለም መንግሥታትን ህግ (የተባበሩት መንግስታትን ቻርተር አንቀጽ 51ን) የጣሰ፥ የሶማሊያ ብሔራዊ ሉዓላዊነትንም የረገጠና እንደ አካባቢያዊ ሰላም አደፍራሽና በጥባጭ የሚቆጠር ሕገ-ወጥ ተግባር ይሆናል::

የሶማሊያ ሁኔታ እጅግ ያሳስበናል፤ የአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጎልብተው እንዲወጡና ሶማሊያ ከገባችበት ቀውስና ከንዑሳን-ጎሳዎችና ከጎሳዎች የእርስ በርስ መፋጀት እንድትላቀቅ፥ ከዚያም ከጎረቤቶቿ ጋር በሰላም ለመኖር እንድትበቃ በጽኑ እንመኛለን:: በአንድ በኩል፥ ይህንን ምኞታችንን የሶማሊያ ሕዝብ በቅጡ እንዲገነዘብልን ስንጥር በሌላው በኩል ደግሞ፥ ካሁን በፊት የሶማሌ አምባገነን ገዢዎች በፈጸሟቸው ስህተቶች በኢትዮጵያና በሶማሊያ ላይ የደረሰው አደጋ እንዳይደገም የሚመለከታቸው ሁሉ ከትንኮሳ እንዲታቀቡ እናስጠነቅቃለን:: ማንኛውም በሶማሊያ ውስጥ መንግሥት የሚይዝ ኃይል አማካይነት በኢትዮጵያ ላይ የተስፋፊነት ወይንም የግዛት ይገባኛልን ጥያቄ ሊያነሳ አይገባም እንላለን:: ሶማሊያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱት የፖለቲካ ኃይሎች ከእንደዚህ ያለ ለአካባቢያችን የሠላም ጠንቅ ከሆነ ለአመርቃዥ ግጭት በር-ከፋች የሆነ ጥያቄ እንዲቆጠቡ እንጠይቃለን እንጅ በይሆናልና በቀድሞ ተከላካይነት ሰበብ ሌላ ሉዓላዊ አገር መውረርን አንደግፍም::

ይህ የነመለስ አሸባሪ ቡድን በሶማሊያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንደቀላል ጉዳይ መታየት የሌለበት፥ ምናልባትም በቀላሉ ልንወጣ ከማንችልበት አካባቢያዊና ውስጣዊ የጦርነት አረንቋ ውስጥ የሚከተንና ኢትዮጵያን ካሁን ቀደም እንደምናውቃት ሆና እንዳናገኛት ሊያደርገን የሚችል አጥፊ እርምጃ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል፡፡

ሃይማኖትን እንደ ምክንያትና እንደመነሻ አድርገው የሚመጡ ግጭቶችና ጦርነቶች ማቆሚያ ሊያጡ፥ ጠቅላላ ኅብረተ-ሰባዊ ክሮችን ሊበጣጥሱና ሊያወሳስቡ የሚችሉ አሉታዊ ክስተቶች እንደሚሆኑ መረዳት ያስፈልጋል፥ ከታሪክም መማር ያሻል፡፡ ብዙውን ጊዜ፥ ኢትዮጵያን እንደ ልዩ አገር እንድትታይ የሚያደርጋት አንዱ ልዩ ባህሪዋ ክርስቲያኖችና እስላሞች በመግባባትና በመረዳዳት ክፉና ደግ ቀኖችን እጅ ለእጅ ተያይዘው አብረው ለመውጣት መቻላቸው እንደሆነ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን፥ ወያኔ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረበት ወቅት አንስቶ በክርስቲያኖችና በእስላሞች መሀል ልዩ ልዩ ጠቦችና ቅራኔዎች እንዲፈጠሩ ለማድረግ ሳያቋርጥ ሲጥር ቆይቷል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን አዋቂና አስተዋይ በመሆኑ፥ እስከዛሬ ድረስ ለሚሸረቡበት ደባዎች ቀላል ሰለባ አልሆነም፡፡ ወያኔ ቢመኘውምና እንዲሆን ቢጥርም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘርና በሃይማኖት ተለያይቶ አልተፋጀለትም፡፡ ዛሬ ታዲያ፥ "የራሷ እያረረባት የሌላውን ታመስላለች" እንዲሉ፥አገር አጥፊው የመለስ ቡድን ውስጣዊ የፖለቲካ ውጥረት ሲያይልበት፥ አንድም የውጭ ጌቶቹን ለማስደሰትና ያስለመዱትን የገንዘብ ድጎማ በኢትዮጵያውያን ደም ለመሸመት፥ በሌላ በኩልም አዲስ ማኅበራዊ ግጭት በማስነሳት የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማበጣበጥና ለማስተራረድ ተነስቷል፡፡ ይህን ታላቅ አገራዊ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል አደገኛ ሴራ በእንጭጩ መቅጨት ለነገ ይዋል ይደር ሊባል የማይችል አገራዊ ግዳጅ ነው፡፡ ስለዚህ እንደዚህ ያለውንም አደጋ ለማስወገድ ብቃት እንዲኖራቸው ነው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች የኅብረት ትግል ለነገ የማይተላለፍ አጣዳፊ አገራዊ ጉዳይ ነው የምንለው፡፡

እንግዲህ፥ ኢትዮጵያን ከገጠሟት ውስጣዊ የኤኮኖሚ፥ የፖለቲካና የማኅበራዊ ችግሮች በተጨማሪ የሠላም ዕጦት፥ አለመረጋጋትና ዕልቂትን ሊያስከትል የሚችል የጦርነት አደጋ እየተከሰተ መሆኑንም ለመጠቆም ሞክረናል፡፡ ዛሬ የሀገራችንን ሕልውና ለማረጋገጥና ለሕዝባችንም ተስፋ ለመስጠት እንዲቻል ወቅቱ የሚጠይቀው የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ተደራጅቶ መታገልና በአንድነት ለመቆም መቻል እንደሆነ አጠያያቂ ሊሆን የሚገባው አይመስለንም፡፡ የኢትዮጵያን ህልውናና የሕዝቧን ሰላማዊ ኑሮና ዕድገት መጠበቅና መንከባከብ ከሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች የሚጠበቅ አገራዊና ብሔራዊ ግዴታ እንደሆነም ለማስገንዘብ ጥረናል፡፡ ይህንንም በተቀላጠፈና በተጠናከረ ሕዝባዊ ኃይል ለማሰኬድ የሚቻለው ደግሞ በተቃዋሚነት የተሠለፉት ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች የኅብረት ትግል እውን ሊሆን ሲችል ብቻም እንደሆነ አስገንዝበናል፡፡ ለዚህም ኢሕአፓ ለረጅም ጊዜ ታግሏል፡፡ ነገር ግን፥ ይህንን የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች የኅብረት ትግል እውን ለማድረግ ለምናደርገው ሙከራ በየመንገዱና በየደረጃው እክሎችና እንቅፋቶች አልተለዩንም፡፡ አሁን በቅርቡ በኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)፥ በኦጋዴን ነጻ አውጭ ግንባር (ኦነአግ)፥ በሲዳማ ነጻ አውጭ ግንባር (ሲነአግ)፥ የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ና በቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ መሀል የተፈረመውና የታወጀው "ትብብር ለነጻነትና ለዴሞክራሲ" በኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅቶች የኅብረት ትግል ላይ እንደመጣ አዲስ አሉታዊ ክስተት ሊጠቀስ የሚችል ምሳሌ ነው፡፡

ኢሕአፓ አባል በሆነበት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) አማካይነት ሰፊና ጠንካራ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅቶች ኅብረት እንዲቋቋም ያልተቆጠበ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ኢዴኃኅም በዚሁ መንፈስ አገራዊ ጥሪ ለሁሉም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች ሲያቀርብ ኦነግ ጥሪውን በአዎንታዊነት ተቀብሎ በአንዳንድ ነጥቦችም ላይ መወያየት ሲጀምር፥ ለማንኛውም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ግራ በሚያጋባ ሁኔታ፥ በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ወኪል ነኝ የሚለው ቡድን ግን በእንደዚህ ዓይነት የአገራዊ ጉዳይ ላይ ለመደራደርና ውሳኔ ለማድረግ "ውክልናውም ሆነ ጊዜው የለንም" በሚል አሉታዊ መልስ

ጥሪውን ሳይቀበለው ቀርቷል። ኅብረት ከኦነግ ጋር የሚያደርገውን ድርድር እየቀጠለ ባለበት አሁንም ለቅን ኢትዮጵያዊ ግራ በሚያጋባ ሁኔታ፥ ቅንጅት የሚገኝበት የድርጅቶች "ትብበር" ለመመስረት ዩትሬክት በምትባለው አንድ የሆላንድ ከተማ ውስጥ በአጭር ጊዜ እንድትገኙ የሚል አፋጣኝ ጥሪ እንደዱብዕዳ ከኦነግ ለኢዴኃኅ ደረሰው። እዚህ ላይ፥ ከዚያ በኋላ የሆነውን እዚህ ላይ ማተት አንሻም። ነገር ግን የስብሰባውን አካሄድና በወቅቱ ኅብረቱ ያደረገው ተሳትፎ፥ በስብሰባው መደምደሚያም ኅብረቱ ለምን የተፈጠረው "ትብብር" አባል መሆን እንዳልፈለገ፥ "ትብብሩ" በዚህ መልክ መቋቋሙና መሠረት ያደረጋቸው ሁለቱ ሰነዶችም የኅብረት ድርጅት ከመመሠረት በላይ በሀገር ደረጃ ያላቸውን አንደምታ አስመልክቶ በጣም ግልጽ በሆነ መልክ ኢዴኃኅ ያብራራበትን የግንቦት 23 1998 ዓም ሰፊ ሰነድ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲያነበው እንጋብዛለን።

ኢሕአፓ፥ የሚታገልለትና እንዲፈጠር የሚፈልገው ትብብር በኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነት፥ ሉዐላዊነትና በሕዝቦችዋ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ፌዴራላዊ እንዲሆንና የዚህ ትብብር አባላት ደግሞ በኢትዮጵያዊነታቸው ሙሉ እምነት ያላቸው ድርጅቶች መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። ከኦነግ ጋር ተጀምሮ የነበረውና በኋላ በታወጀው "ትብብር" የተጨናገፈው ድርድር ሲያውጠነጥን የነበረው በነዚህ መሠረታዊ የአገር ሉዓላዊነት፥ የሕዝብ እኩልነትና አንድነት ጥያቄ ዙሪያ ነበር። ኅብረቱም በተደጋጋሚ እንደሚያስረዳው ኢሕአፓም እንደሚያምንበት፥ በተለያዩ የሀገሪቷ መሠረታዊ ለውጥ ፈላጊ ኃይሎች መሀል የሚደረገው የመተባበር ጥረት፥ በመጪዋ ኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ሂደትን የሚያጠናክር፥ ዘለቄታዊ ሰላምን የሚያጎናጽፍ እንዲሆን ታስቦ መካሄድ ይኖርበታል።

በዛሬው ወቅት ሀገራችንን ቀስፈው የያዙዋት ችግሮች ከባድ፥ እጅግ የተወሳሰቡና የተቆላለፉ መሆናቸውን አይተናል። ምንም ትልቅና ኃያል ቢሆኑም እንኳን ጥቂት ድርጅቶች ብቻቸውን በመሆን ችግሮቹን እንኳን ሊያስወግዱ በመጠኑም ሊቀርፉ አይችሉም። ትናንትም፥ ዛሬም ያለማቋረጥ የሚስተጋባው የኢትዮጵያ ሕዝብ የድርጅቶች ኅብረት ጥያቄ ሙሉ ለሙሉ መልስ ማግኘት ይኖርበታል። ይህ ሕዝባችን የሚፈልገው ዓይነት የትግል አንድነት ደግሞ ኩሬን በማያዘልል ብልጣብልጥነት ወይም በማንአህሎኝነት ሊፈጠር አይችልም። የአገር ጉዳይ ማንም ግለሰብ ወይም ድርጅት እንደግል ንብረቱ በሞኖፖል የሚወስንበት ወይም በይደር የሚያስተላልፈውም ጉዳይ አይደለም። የሚደረጉት የፖለቲካ ውሳኔዎች በሙሉ ከፍተኛ ትርጉምና ዋጋም አላቸው። የሚመነዘሩት በንጹሀን የኢትዮጵያ ሕዝብ ህይወት መሆኑ ግልጥ ሊሆን ይገባል። ይዋል ይደር እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብም በስሙና በምትኩ ስለሚወሰኑበትና ስለሚወሰኑለት ውሳኔዎች መጠየቁ አይቀርም።

ስለዚህ፥ ትክክለኛውን ነገር ከወዲሁ መጀመር አንድም ብልህነት፥ በሌላ ገጹም አገርና ሕዝብ ወዳድነት ይሆናል። ባጠቃላይ ይህ አሁን የኅብረት ትግላችን ያለበት ደረጃ ከፍ እንዲል፥ በ"ትብብሩ" በኩል ሁኔታው እንዲቀየር ሐቀኛ ፍላጎት ካለ በተለይ፥ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ለትብብሩ ከሁለት ወራት በፊት ላቀረባቸው ቀጥተኛ ጥያቄዎች የሚመለከታቸው ድርጅቶች ቀጥተኛ መልስ ይሰጡ፥ ግልጥና ዴሞክራሲያዊ የሆነ ውይይትና ድርድር አሁኑኑ ይጀመር፥ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት፥ ታዋቂ ግለሰቦችና የአገር ሽማግሌዎች የሚሳተፉበት አጠቃላይ ስብሰባ በአፋጣኝ ይዘጋጅና ይጠራ የሚለውን አቋምና ጥሪ ኢሕአፓ ይደግፋል።

## የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ ትግል ድልን ይጎናጸፋል!

## በእኩልነትና በመከባበር ላይ ለቆመች ኢትዮጵያ ሁላችንም በጋራ እንታገል፥ ዘብ እንቁም!!